Skolverket

**አሳዳጊ ወላጆች ለሆናችሁ**

## Prao - ለስራ ህይወት እና ለተጨማሪ ጥናቶች አስፈላጊ ዝግጅት

በቅርቡ ልጅዎ prao ለማድረግ ጊዜው ይሆናል!

Prao እንደ ተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ ይገለጻል እና ተማሪዎቹ በስራ ቦታ መስራት ምን እንደሚመስል እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል። ሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት እና የልዩ ፍላጎት አጠቃላይ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በ8 እና/ወይም 9ኛ ክፍል ተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ መውሰድ አለባቸው። በስዊድን የትምህርት ሕግ ላይም እንዲሁ ተገልጿል።

ለወደፊት ጥሩ ምርጫዎችን ለማድረግ ልጅዎ ስለ የስራ ገበያ እውቀት እና በተለያዩ የሙያ ዘርፎች እና ኢንዱስትሪዎች ልምድ ማግኘቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ (Prao) ልጅዎ በስራ ህይወት ውስጥ የትኞቹ ክህሎቶች እና ችሎታዎች እንደሚያስፈልገው እንዲያውቅ ያመቻችልዎታል። የችሎታ ምሳሌዎች ተነሳሽነት እና ኃላፊነት መውሰድ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ሁሉም ተማሪዎች ተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫን (Prao) መፈጸም አለባቸው።

ትምህርት ቤቱ እና የስራ ቦታው የልጅዎ የተግባር የስራ ህይወት አቅጣጫ ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ይተባበራሉ። ይህ ለምሳሌ፣ ልጅዎን በስራ ቦታ የሚደግፉ ሞግዚቶችን መሾም እና ቀጣሪዎች የስራ ሰዓቱን እና የስራ አካባቢን በተመለከተ ህጎችን መከተላቸውን ማረጋገጥን ሊያካትት ይችላል። በተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ ወቅት ልጅዎ በትምህርት ቤቱ በኩል ዋስትና ተሰጥቶታል።

ትምህርት ቤቱ ልጅዎ ለተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ ጊዜ በሚገባ ዝግጁ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። ብዙውን ጊዜ፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራት ተሰጥቷቸዋል። በዚህ መንገድ በክፍል ጓደኞቻቸው በኩል ስለሌሎች የስራ ቦታዎች እና ሙያዊ ቦታዎች እውቀት ያገኛሉ።

ስለተግባራዊ የስራ ህይወት አቅጣጫ (Prao) የበለጠ ማወቅ ከፈለጋችሁ እባኮትን የትምህርት ቤቱን የጥናት እና የስራ አማካሪ ወይም አስተማሪን ያነጋግሩ።

Skolverket

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚያነጋግሩት ሰው

.....................................................................................................

ስልክ ቁጥር

.....................................................................................................

የኢሜል አድራሻ:

.....................................................................................................



